በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS
የፕሬስ መግለጫ PRESS RELEASE

# የኢትዮጵያና ኩዌት ወዳጅነት ተምሳሌታዊ ነው፡፡

የእኩዌትና የኢትዮጵያ ግንኙነት ጠንካራና ለሌሎች ምሳሌ ሊሆን የሚችል መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ገለፁ። ዶ/ር ወርቅነህ ከኩዌት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሼክ ሳባህ ካሊድ አልሳባህ ጋር ተገናኝተው በተነጋገሩበት ወቅት በፖለቲካና በዲፐሎማሲ መስክ ያለውን ጠንካራ ግንኙነት በንግድና ኢንቨስትመንት መስክ የበለጠ ሊጎለብት እንደሚገባ የኩዌት ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በግብርና እና የግብርና ውጤቶቻችን በማቀናባበር መስክ ተሳትፎ በሚያደርጉባቸው ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል፡፡ ኢትዮ-ኩዌት የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ስብሰባ በመጪው መስከረም እንዲካሄድ የጋራ መግባባት ላይ ላይ ተደርሷል፡፡

ሼክ ሳባህ ካሊድ አልሳባህ ባደረጉት ንግግር ኩዌት በሳዳም ሁሴን አስተዳደር በተወረረችበት ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት እና ህዝብ በሰጡት ድጋፍ ባለውለታችን ናቸው ብለዋል፡፡

የኩዌቱ አሚር H.H. Sheikh Sabah Al-Ahmad Al-Jaber Al-Sabah ክቡር የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት በተለያዩ ወንጀሎች ተከሰው ለነበሩ ኢትዮጵያውያን ምህረት አድርገዋል፡፡ በኩዌት ጉብኝት ያደረጉት ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁም በራሳቸውና በኢፌዲሪ መንግስት ስም ለተሰጠው ምህረት ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ በውጭ አገር የሚገኙ ወገኖችን በአገራቸው የሚካሄደውን የልማት ጥረት እንዲደግፉ ጠየቁ፡፡ ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ በኩዌት ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያዊን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ጋር ባደረጉት ውይይት፣ ወደ መካከለኛው ምስራቅ አገሮች የስራ ስምሪት የሚያደርጉ ወገኖቻችን ተገቢው ክህሎት እንዲኖራቸው እንደሚደረግና መንግስት መብታቸውን ለማስከበር እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በወቅቱ ከወራት በፊት ከአሰሪዋ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ከ7ኛ ፎቅ ወድቃ ህይወቷ የተረፈውን ወ/ት ታደሰች ሳዲቅን ያነጋገሩ ሲሆን ወደ አገሯ እንድትመለስ ድጋፍ እንደሚደረግላት ቃል ገብተዋል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ሰኔ 13 ቀን 2009 ዓ.ም.**